GSMA

# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ
ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

# ሞጁል 7:- TikTok

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መረጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

# ይህ ምንድን ነው?

**በስልኩ ላይ TikTok ያሳዩ።**

**ያብራሩ፡-** «TikTok ቪድዮዎችን እንዲመለከቱ፣ እንዲፈጥሩ ወይም እንዲያጋሩ የሚደርግ በስልክዎ ላይ ያለ መተግበሪያ ነው። እንደ YouTube፣ Facebook ወይም ቴሌቪዥን ያለ ነው፣ ነገር ግን በተለምዶ ቪድዮዎቹ በጣም አጭር ናቸው።»

«እነዚህ ቪድዮዎች በዓለም ዙሪያ ባሉ ሰዎች የተሰሩ ናቸው – አንዳንዳንዶቹን ሊያውቋቸው ይችላሉ፣ ነገር ግን አንዳንዶቹን አያውቋቸውም። እነዚህን ቪድዮዎች የሰሩት እንደ እርስዎ እና እንደ እኔ ያሉ ሰዎች ናቸው።»

«እነዚህ ቪድዮዎች ስለሁሉም ነገር ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኛዎቹ ቪድዮዎች ስለ ዜናዎች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ ሙዚቃ ወይም ስፖርት ናቸው፣ ነገር ግን ሌሎች ቪድዮዎች ስለ ንግድዎ፣ ምግብ ስለመስራት፣ ቤተሰብዎን ስለመንከባከብ ወይም እርሻዎን ለመንከባከብ የሚረዱ አዳዲስ ነገሮችን እንዲማሩ ያግዛሉ።»

# የሚያስፈልጉዎ ቁሳቁሶች፡-



ስማርት ስልክ ቀፎዎች




የTikTok ፖስተሮች




የደህንነት ፖስተር

# ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ያብራሩ** «TikTok ላይ ስለሚወዱት ስፖርት፣ ሙዚቃ ወይም ዳንስ ቪድዮዎችን መመልከት ይችላሉ፣ ነገር ግን በጣም ብዙ ተጨማሪ ነገሮች ያገኛሉ! ለምሳሌ፣ አንድ የተወሰነ ጥራጥሬ (ለምሳሌ፣ በቆሎ) እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል፣ አንድ የተወሰነ የምግብ ዓይነትን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ወይም ለልጆችዎ የሚሆኑ ትምህርታዊ ቪድዮዎችን ወይም እራስዎን አዳዲስ ክህሎቶችን ለማስተማር ወይም አዲስ መረጃ ለማጋራት የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮችን ሊያገኙ ይችላሉ።»

የ«TikTok ጥቅም ቪድዮዎችን ለመመልከት ብቻ አይደለም፣ እርስዎም የራስዎን ቪድዮዎች መፍጠር ይችላሉ። የTikTok ቪድዮዎችን የሚሰሩ ሰዎች ልክ እንደ እኔ እና እንደ እርስዎ ናቸው!»

ስለ TikTok ጥቅሞች እና በግልዎ እንዴት እንደሚጠቀሙበት የራስዎን ምሳሌዎች ለሰልጣኙ ያጋሩ።

**ለሰልጣኙ ሕይወት እንዴት** ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል በመወያየት ከሰልጣኙ ጋር የሚገናኝ እንዲሆን ያድርጉት። ለሚከተሉት የሰልጣኝ ዓይነቶች ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን ታሳቢ ያድርጉ፦

**አዛውንት፦** ርቀው በሚኖሩ ጓደኞች እና ቤተሰብ የተለጠፉ ቪድዮዎችን፤ የፊልም ቅንጭቦችን፣ መንፈሳዊ ስብከቶችን ወይም ዜናዎችን ይመለከቱ።

**እናት ወይም የቤት እመቤት፦** ለቤተሰብዎ የሆነ ምግብ እንዴት እንደሚያዘጋጁ ይማሩ፤ ልጆችዎ በትምህርታቸው የተሻለ እንዲሰሩ እና የቤት ሥራቸውን እንዲያጠናቅቁ ይደግፉ፤ ቤትዎን ለመንከባከብ ጠቃሚ ምክሮችን እና ብልሃቶችን ያግኙ።

**የንግድ ባለቤት፦** ንግድዎን ለማሳደግ የሆነ ምግብ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ይማሩ፤ ለንግድዎ ድጋፍ ለማድረግ ስለ ንግድ አስተዳደር፣ አዝማሚያዎች እና ዕቅዶች መረጃዎች ያግኙ፤ ንግድዎን ለማሳደግ ስለ ንግድ ስራ ምክሮችን እና አነቃቂ ሃሳቦችን ያግኙ።

**ገበሬ ወይም የገጠር ሰው፦** አንድ የሆነ ጥራጥሬ እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል ይማሩ (ለምሳሌ፣ ቲማቲም ወይም በቆሎ የመሳሰሉ ነገሮችን በሆነ ወቅት እንዴት መዝራት እንደሚቻል) ወይም አንድ የተወሰነ ተባይን እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ጠቃሚ ምክሮች።

**ወጣት፦** የሚወዱትን የእጅ ሥራ እንዴት መስራት እንደሚቻል እና ገንዘብ እንዴት እንደሚያገኙ ይማሩ (ለምሳሌ፣ ሜካፕ፣ የእንጨት ሥራ ወይም የልብስ ስፌት)፤ የትምህርት ቤት ሥራዎችን ለማጠናቀቅ የሚያግዙ ቪድዮዎችን ይመልከቱ፤ የስፖርት ቅንጭቦችን፣ አስቂኝ ቪድዮዎችን ወይም አጋዥ ሥልጠናዎችን ይመልከቱ።

# እንዴት ነው የሚሰራው?

## ስልኩን በሰልጣኙ እጅ ላይ ያድርጉት እና ቅደም ተከተሎችን እንዲከተሉ ያግዟቸው።

**ይጠይቁ** «ይህ ምን እንደሆነ ያውቃሉ? ለምን ይጠቅማል? በስልክዎ ላይ ሊያገኙት ይችላሉ?»

በስልኩ ላይ TikTokን እንዴት ማግኘት እና መክፈት እንደሚችሉ **ያብራሩ።**

**ያብራሩ፡-** «ፍላጎት የሚያሳድሩባቸውን ቪዲዮዎችን እና መረጃዎችን ለማግኘት፣ TikTok ላይ ነገሮችን መፈለግ ይችላሉ። ፍለጋን በመጠቀም፣ TikTok ለመመልከት የሚወዷቸውን ነገሮች ያሳይዎታል።»




**«TikTok ላይ ቪድዮዎችን እንዴት መፈለግ እንደሚቻል»** ፖስተርን በመጠቀም፣ TikTok ላይ ቪድዮዎችን እንዴት መፈለግ እንደሚቻል ያብራሩ፡፡

- ከማያ ገጹ ከላይ በስተቀኝ በኩል ያለውን የፍለጋ ምልክት ጠቅ ያድርጉት።
- የፍለጋ ቃል ወይም ሐረግ ወደ አሞሌው ያስገቡ። ሰልጣኞች ፍላጐት ያሳደረባቸውን ነገር እንዲፈልጉ ይፍቀዱላቸው። የሚፈልጉትን እንዴት በተሻለ መንገድ ማግኘት እንደሚችሉ መምራት ይችላሉ (ለምሳሌ ቁልፍ ቃላትን ስለመጠቀም)። ለምሳሌ ተባዮችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል፣ እነሱ የሚወዱትን ምግብ እንዴት ማብሰል እንደሚቻል፣ ወይም እንዴት ኳስ ማንጠባጠብ መማር እንደሚችል ፍለጋ ሊያደርጉ ይችላሉ።
- ከቪድዮዎቹ አንዱን ይምረጡ። ያስታውሱ ምርጡን ቪድዮ ለማግኘት ወደታች መውረድ ሊኖርብዎ ይችላል።

**ይጠይቁ፡-** «TikTok ላይ የትኞቹን ቪድዮዎችን ሊመለከቱ ይወዳሉ?»

TikTok ላይ እንደሚገኙ ላያውቁ የሚችሏቸውን ቪዲዮዎች እንዲፈልጉ ያግዟቸው። ከነዚህም መካከል የምግብ የማብሰል ቪድዮዎችን፣ የልጆች ትምህርታዊ ቪድዮዎችን ወይም አንድን ነገር እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል (ለምሳሌ፣ ብስክሌት ወይም የውሃ መስመር ፍሳሽ) የሚያብራሩ ቪድዮዎችን ወይም እርስዎ (አሰልጣኙ) በተለየ መንገድ ፍላጎት ያሳደረባችሁን ነገር ሊያካትት ይችላል።

## ልምምድ ያድርጉ!

**አሁን ስለ TikTok አውቀዋል፣ ስለምን ለማወቅ ፍላጎት አደረብዎት?»**

በፍላጎታቸው መሠረት ሰልጣኙን ለመፈለግ የሚፈልጓቸውን አንዳንድ ቁልፍ ቃላትን **ይጠይቁ**። አንድ ወይም ሁለት ቃላትን በመጠቀም ፍለጋውን ቀላል ለማድረግ ይሞክሩ።

**ጠቃሚ ምክር፡-** «ያስታውሱ የTikTok ቪዲዮዎችን መመልከት በጣም አስደሳች ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ብዙ የTikTok ቪድዮዎችን መመልከት ብዙ የተንቀሳቃሽ ስልክ ውሂብ/ክሬዲትን ይጠቀማል ስለዚህ ብዙ ውሂብ ሊፈጅ ስለሚችል በመመልከት ምን ያህል ጊዜ እንደሚያጠፉ ይጠንቀቁ። TikTok ላይ ቪዲዮዎችን በመመልከት የሚያጠፉትን ጊዜ ለመገደብ ያስቡበት።»

**ጠቃሚ ምክር፡-** «ቪድዮዎችን መመልከት እና መስራት የሚችሉባቸው ሌሎች እንደ TikTok ያሉ መተግበሪያዎች አሉ ለምሳሌ፣ Instagram፣ Snapchat ወይም YouTube። በእነዚህ መተግበሪያዎች ላይ፣ ልክ እንደ TikTok ሁሉ፣ በቪድዮው ውስጥ ያሉ በርካታ ሰዎች እንደ እርስዎ ናቸው።»

## ደህንነት

«TikTok አስደሳች መተግበሪያ ሲሆን፣ ብዙ ነገሮችን ሊያገኙበት ይችላሉ። TikTok እና መላው በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም እራስዎን በመጠበቅ እና በመተግበሪያው ላይ ለሚያስቀምጡት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።»

«ያስታውሱ፣ TikTok ላይ ያሉ ቪድዮዎች በሰዎች የተፈጠሩ ናቸው፣ አንዳንዶቹ ልክ እንደ እርስዎ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። TikTok ላይ የሚመለከቱት ሁሉ እውነት አይደለም፣ ስለዚህ ቪድዮዎቹን በተመለከተ ምንም ነገር ከማድረግዎ ወይም ከማጋራትዎ በፊት ደግመው ያስቡ።»




**«በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

እነዚህ ጠቃሚ ምክሮች TikTok ሲጠቀሙ ምን ማለት እንደሆኑ ከሰልጣኝዎ ጋር **ይወያዩ**።

ለሰልጣኝዎ ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን በመጠቀም ጠቃሚ ምክሮቹ ህይወት እንዲኖራቸው ያድርጉ። ለምሳሌ፣ የተወሰኑ ሰዎች TikTok ላይ ስለሚገኙ አንዳንድ ይዘቶች ሊጨነቁ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች TikTokን ስለሚጠቀሙ አጭበርባሪዎች ሊጨነቁ ይችላሉ፤ አንዳንድ ሴቶች ደግሞ ትንኮሳን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ የበለጠ ሊያሳስባቸው ይችላል።

አጭር ሥልጠና፡-

**TikTok**

# ፖስተሮች እና ተቆርጠው የወጡ ማሳያዎች

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

GSMA

# በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች

**በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ያስታውሱ፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም ራስዎን በመጠበቅ እና በመስመር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።**

## በመስመር ላይ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ያስታውሱ

ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር በመስመር ላይ መለጠፍ ይችላል፣ ስለዚህ የሚመለከቱትን ሁሉ አይመኑ። ከሚያምኑት ሰው እንኳን ቢሆን እውነት ላይሆን ይችላል። መረጃን ለሌሎች ከማጋራትዎ በፊት ጥንቃቄ ያድርጉ።

## በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው ገንዘብ ከመላክዎ በፊት ደግመው ያስቡ

ያልጠየቋቸውን ኢሜይሎች፣ መልዕክቶች ወይም ብቅ-ባዮች በተለይም ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆኑ ወይም እንግዳ የሆኑ አገናኞችን ከያዙ ይጠንቀቋቸው።

## የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ የግል መረጃዎን ለግልዎ ያቆዩ

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር፣ እንደ ሙሉ ስምዎ፣ የቤት አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ያሉ የግል ዝርዝሮች ማጋራት የለብዎትም።

## በመስመር ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት አያድርሱ

መልካምነትን እና አክብሮትን ያሳዩ። ጉልበተኝነት አያሳዩ፣ የውሸት መረጃን አያሰራጩ ወይም ማንም ሰው ላይ ትንኮሳ አያድርሱ። በመስመር ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእውነተኛ ሕይወት ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

## ማጭበርበሮችን እና አጭበርባሪዎችን ይወቁ

ልክ በእውነተኛ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ በበይነመረብ ላይም ሌቦች እና ወንጀለኞች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በመስመር ላይ ሌላ ሰው እንደሆኑ ያስመስላሉ።

## የሚያስቸግርዎትን ሰው በማገድ ወይም ችላ በማለት እርምጃ ይውሰዱ

የሆነ ሰው በመስመር ላይ ካስቸገረዎ ወይም ትንኮሳ ካደረሰብዎ፣ እርዳታ ይጠይቁ እንዲሁም ለሆነ ሰው ይናገሩ ወይም ሪፖርት ያድርጉ።

# የዳታ ወጪዎች



TikTok
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# በTikTok ላይ ቪድዮዎችን እንዴት መፈለግ እንደሚቻል

1




2




3



TikTok
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# የTikTok «ለእርስዎ» ገጽን መረዳት




**ፍለጋ፦**
የሚወዱትን ቪድዮ ያግኙ።

**የይዘት ፈጣሪ መገለጫ፦**
የይዘት ፈጣሪ ቪድዮውን የሠራው ሰው ነው። እንደዚህ ያሉ ተጨማሪ ቪድዮዎችን ማግኘት ይችላሉ።

**መውደድ፦** የልብ ምልክትን መጫን ማለት ቪድዮውን «መውደድ» ማለት ነው። «መውደድ» የሚለውን ከተጫኑ ተመሳሳይ ቪድዮዎችን ያገኛሉ። ቁጥሩ ምን ያህል ሰዎች እንደወደዱት የሚያሳይ ነው!

ስለዚህ ቪድዮ የሆነ ነገር ለማለት ከፈለጉ **አስተያየት** ይስጡ ወይም ሌሎች ያሉትን ይመልከቱ። ቁጥሩ ምን ያህል ሰዎች አስተያየት እንደሰጡ ነው።

**ተወዳጅ፦** ይህን ቪድዮ «ተወዳጅ» ማድረግ በኋላ ላይ እንደገና ለመመልከት ዝርዝር ውስጥ ማስቀመጥ ማለት ነው።

**ማጋራት፦** ይህን ቪድዮ በWhatsApp ጨምሮ ለጓደኞችዎ ወይም ለቤተሰብዎ መላክ ይችላሉ

**ወደ ላይ ማንሸራተት፦**
በማያ ገጹ ላይ ጣትዎን ወደላይ ካንቀሳቀሱ ወደሚቀጥለው ቪድዮ ይሄዳሉ!

**ወደ ታች ማንሸራተት፦**
የመጨረሻውን ቪድዮ እንደገና መመልከት ከፈለጉ በማያ ገጹ ላይ ጣትዎን ወደታች ማንሸራተት ይችላሉ

TikTok
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# በTikTok ላይ ቪድዮን እንዴት «ተወዳጅ» ማድረግ እንደሚቻል

1




2




3



# በTikTok ላይ ቪድዮን እንዴት «ተወዳጅ» ማድረግ እንደሚቻል

1




2




3



TikTok
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# በTikTok ላይ ቪድዮን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል

1




2




4




5



TikTok
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# በTikTok ውስጥ «የአየር ሰዓት ቆጣቢ» ሁነታን ማብራት



TikTok
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# ለምን ይህን ቪድዮ ይመለከታሉ

1




2




3



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

TikTok

